

# በሎስአንጀለስ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በሶማሊያ የአሸባሪ ሀይልና በፀረ- ሠላም ሀይሎች የኢትዮጵያ መንግሥትና ጀግናው የመከላከያ ሠራዊት የወሰዱትን እርምጃ ደገፉ

በሎስአንጀለስ የሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት በሎስአንጀለስ ከተማና አካባቢው ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጥር 12 ቀን 1999 ዓ.ም በጠራው ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥትና የመከላከያ ሠራዊት የሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት ብሎ በሚጠራው ስብስብ ውስጥ እራሳቸውን የሰገሰጉ አለም አቀፍ ሽብርተኞች፣ የሻዕብያ ጀሌዎችና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆኑ ሀይሎችን ለመደምሰስ የወሰዱትን እርምጃና ያስገኙትን አኩሪ ድል በሚመለከት ውይይት አካሄዱ፣ የድጋፍ መግለጫም አወጡ

በዚሁ ስብስባ ላይ በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ ቆንስላ ጄኔራል አምባሳደር ክቡር አቶ ታዬ አፅቀሥላሴና በጽ/ቤቱ የኮሙኒቲ ጉዳዮች ክፍል ሃላፊ የሆኑት አቶ እንዳለው ምትኩ የእስላማዊ ምክር ቤትና አለም አቀፍ የጂሀዲስት ቡድኖች በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ ላይ ጋርጠውት ስለነበረው አደጋ፣ የአገራችን ደመኛ ጠላት የሆነው የሻዕቢያ ቡድን አፍሪካ ቀንድን ለማተራመስ በመፈጸም ላይ ስላለው እኩይ ተግባርና በሶማሊያ ውስጥ ስለነበረው አፍራሽ ተልዕኮ፣ የኢትዮጵያ መንግሥትና የመከላከያ ሠራዊታችን በጥልቅ ጥናት፣ ወታደራዊ ዝግጅትና ግልፅ ተልዕኮ ላይ በመመሥረት የወሰዱትን ፈጣንና ወሳኝ እርምጃ በሚመለከት መግለጫ ሰጥተዋል።

የስብሰባው ተሳታፊዎችም በቀረቡት የመወያያ ሀሳቦች ላይ ሰፋ ያለ ውይይት በማካሄድ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥተዋል፡-

1. በሶማሊያ የነበረው የእስልምና ም/ቤትና በዙሪያው የታቀፉ የአለምአቀፍ ሽብርተኞችና ፀረ-ሠላም ሀይሎች በአገራችን ላይ እያደረሱ የነበረውን የአሻባሪ ተግባር ለመመከትና ለመደምሰስ የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያስተላለፈውን ውሳኔ እንደግፋለን፣ በቀጣይነትም የህዝባችንና የአገራችንን አንድነት ለማስከበር በሚደረገው ትግል ውስጥ የበኩላችንን አተዋጽኦ ለማድረግ ቆርጠን መነሳታችንን እናረጋግጣለን።

2. የኢትዮጵያ መንግሥት የአገራችንና የህዝባችንን ደህንነት ለመጠበቅ ሲከተለው የቆውንና በስጋት ትንተና ላይ የተመሠረተ የአደጋ ተጋላጭነት የመቀነስ ስትራቴጂ አንድነትን፣ በቀጣይነትም የአገራችንን ህልውና የሚፈታተኑ ፀረ-ሠላምና ፀረ-አንድነት ሀይሎችን የመከታተልና የመመከት ተግባሩን አጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን።

3. የአገራችንን አንድነትና ብሔራዊ ደህንነት ለመጠበቅ የተሰጠውን ህዝባዊ ተልዕኮ በጥበብና በቆራጥነት በመፈጸም ላይ ለሚገኘውና አኩሪ መመኪያና አለኝታ ለሆነው የኢትዮጵያ መከላከያ ሀይል ሙሉ ድጋፋችንን እንሰጣለን፣ ምስጋናችንንም ለሠራዊት እንዲቀርብልን እንጠይቃለን።

4. በውጭ አገር ተቀምጠው በኢትዮጵያ ስም እየማሉና እየተገዘቱ ነገር ግን የአገራቸውን ስምና ሞገስ በማንኳሰስና በማንቋሸሽ ላይ የተሰማሩ የተቋዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከዚህ ተግባራቸው እንዲታቀቡ፣ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊው በፈለገውና በመረጠው የስብሰባ መድረክ እንዳይገኝና እንዳይሳተፍ የሚያሸማቅቁ፣ የሚሳደቡ፣ ዛቻና ማስፈራራት የሚፈጽሙ ነውጠኛ ግለሰቦችና የድርጅት መሪዎች ከዚህ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ ጥሪ አናቀርባለን።



